

በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከጁን 1-30/2025 የነበረዉ የአየር ጠባይ ግምግማ እንዲሁም

# ከጁላይ 1-31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና

# ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2025

አዲስ አበባ


## 1.2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ጠባይ

ባለፈዉ የጁን ወር በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እና በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ አና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በሀዋሳ 22፣ በባህር ዳር 21፣ ደብረ ማርቆስ 25፣ ቢሾፍቱ 24.2፣ ጎንደር 29.4፣ ጎሬ 31.4፣ 25፣ 23.3፣ 21.7፣ 43.9፣ 21፣ ጅማ 39.4፣ 22፣ 50፣ ነቀምት 31.4፣ 44.6፣ 69፣ 27.3፣ 54.5፣ 35.3፣ 71፣ 27.2፣ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 30.8፣ አቦቦ፣ 38፣ አዴት 20.4፣ አይራ 23.4፣ 28.5፣ 20.6፣ 64.6፣ 32፣ 31.4፣ አማን 23.4፣ 25.4፣ 21.9፣ 53.4፣ 43.4፣ 30.8፣ አንገር ጉቲን 38፣ 54.2፣ 32፣ 26.4፣ 30.4፣ 23.2፣ 59፣ 25.6፣ 36.4፣ አርጆ 26.2፣ 28.4፣ 26.4፣ 24.2፣ 28.6፣ 20.2፣ 22.8፣ አየሁ 52.6፣ አይከል 25.3፣ 23.4፣ በደሌ 24፣ 21.3፣ 37፣ 46.4፣ 37.8፣ ብላቴ 36.5፣ 27.2፣ ቦሬ 47.2፣ 50.9፣ 24.8፣ በሂ 32.8፣ 35.3፣ ቡለን 2420.3፣ 30.3፣ 20.8፣ ፣ ቡርጂ 21.1፣ ቻግኒ 22.2፣ 23.2፣ 50.6፣ 31.7፣ 21.6፣ ጨዋቃ 25.6፣ 20.2፣ 38፣ 22፣ 32፣ 26.3፣ 24.2፣ 26.7፣ 26.6፣ ጭራ 21.5፣ 25.4፣ 49.9፣ 22፣ ዳንግላ 20.1፣ 66፣ ደባርቅ 33.1፣ 21.3፣ ደብረ ታቦር 31.7፣ ደምቢ ዶሎ 42.8፣ 28.8፣ 33.5፣ ዲላ 18.8፣ 19.4፣ 35.2፣ 25.2፣ ኢጃጂ 26.2፣ 21.5፣ 26.6፣ 25.7፣ 30.8፣ ፉኙዶ 26፣ 23፣ 37፣ 32፣ 40፣ ጋምቤላ 21.2፣ 34.5፣ 32.2፣ 26.6፣ 24.4፣ 22.4፣ 20.4፣ ጋቲራ 18.6፣ 33.4፣ 33.4፣ 44.6፣ 29.3፣ 25.7፣ 34.6፣ 26.4፣ 28.8፣ ወሊሶ 25.1፣ 43.2፣ ጊዳ አያና 32.1፣ 21.6፣ 23.5፣ 62.3፣ 42፣ 26.4፣ ጊምቢ 36.6፣ 26.7፣ 32.5፣ 28.1፣ 34.7፣ 35.9፣ 21.3፣ ሆሳዕና 22.4፣ እምድብር 26.1፣ 24፣ 21.2፣ ጅግጅጋ 20.5፣ 20.8፣ ጅንካ 60.7፣ 38.8፣ ካቺሴ 40፣ 30፣ 62.3፣ ቁሉምሳ 31.5፣ ላይብር 20.1፣ ሊሙ ገነት 22.5፣ 60፣ 23.8፣ ማንኩሽ 23.5፣ 30፣ 60.4፣ 30፣ 50.6፣ 36.4፣ ማሻ 34.5፣ 26.6፣ 30፣ መተማ 42፣ አዳማ 29.4፣ ነጆ 24.2፣ 23.5፣ 34.5፣ 21፣ 56.8፣ 25.5፣ ፓዌ 26.7 ሰኮሩ 41.2፣ 23፣ 24.4፣ ሻዉራ 20.9፣ እንዲሁም ሻምቡ 47.3፣ 27.4፣ ሽርቆሌ 43.4፣ ቴፒ 55.8፣ ተርጫ 23.2፣ ወራቤ 23.2፣ ወላይታ 21.9፣ 24.3፣ 22.2፣ የትኖራ 21.5፣ አቦ ሞሪጋ 32.2፣ 37.2፣ 25.6፣ እብናት 32.4፣ ኖፓ 25.8፣ ኦሞ ናዳ 26.6፣ ጊናግር 22.4፣ ሙጊ 27.6፣ ፊንጫ 22.7 እንዲሁም ሽንዲ 20.5፣ 26 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በአጠቃላይ ባለፈዉ የጁን ወር በ45 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40.0 እስከ 71 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ነቀምት፣ ዳንግላ፣ ካቺሴ፣ ጂንካ፣ ሊሙ ገነት፣ ጅማ፣ ጭራ፣ በደሌ፣ ጎሬ፣ ወሊሶ፣ ፉኙንዶ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡





ምስል፡1 ከጁን 1-30 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉዉ የጁን ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ሰሜን፣ ምዕራብና የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ወላይታ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ ከ51-509 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ9-27 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

ባለፈዉ የጁን ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ሰሜን፣ ምዕራብና የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ወላይታ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል በሰመራ፣ ገዋኔ፣ መተሃራ፣ አዋሽ አርባ፣ አይሻ፣ መተማ፣ ጭፍራ፣ ድሬ ዳዋ፣ ዳሊፋጊ፣ ፉኙዶ፣ ሽዋ ሮቢት፣ ጨፋ፣ ጎዴ፣ ቀበሪዳሀር፣ ማጀቴ፣ ኑራ ኤራ፣ መኢሶ፣ ሻዉራ፣ ማይጨዉ፣ ባቲ፣ አቦቦ፣ ጋምቤላ፣ አቦምሳ፣ ጨዋቃ፣ ሽርቀሌ፣ ኮምቦልቻ፣ ስሪንቃ፣ አይደር፣ አዳሚ፣ አለም ከተማ፣ ፊቼ፣ ሽሬ፣ ቴፒ፣ ሰዉላ እና ፓዊ፣ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 33.2 እስከ 45.8 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል፡፡





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር

## 1.3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጁን ወር በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቦታ ቦታ በመጠን ቢለያይም በስርጭት ረገድ አብዛኛዉን ቦታ ያዳረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበረ (ካርታ 4)፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከጁን ወር ጀምሮ የዘር ጊዜና የማሳ ዝግጅት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች በወቅቱ ለመዝራት አመቺ ሁኔታ የፈጠረ ሲሆን፤ ዘግይተዉ ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች የውኃ ፍላጎታቸውን እንዲያሟሉና ዕድገታቸዉን እንዲቀጥሉ አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በተጨማሪም የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተገኘው መጠነኛ እርጥበት ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር ልምላሜ ጥሩ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ ተከታታይነት የነበረው ዝናብ በአብዛኛው ለግብርና ስራ አንቅስቃሴ አዎንታዊ ነበረ (ካርታ 4)።



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.4 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው

ባሳለፍነው የጁን ወር በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ባሮ አኮቦ፣ አይሻ፣ ኦጋዴን፣ መካከለኛ እና ታችኛው ተከዜ፣ በላይኛው፣ መካከለኛ እና ደቡባዊ ታችኛው አዋሽ፣ በላይኛው ገናሌ ዳዋ እና ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው(ካርታ 5)፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በላይኛው እና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ በመካከለኛው እና ታችኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ እንዲሁም በጥቂት በመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ ገናሌ ዳዋ፣ መረብ ጋሽ፣ በላይኛው ተከዜ እና በታችኛው ምስራቃዊ አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ዝቅተኛ እርጥበትና ከፍተኛ ትነት ተስተውሎባቸዋል (ካርታ 5)።



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁን ወር ውስጥ የተቀሩትን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ሙሉ በሙሉ ያዳርሳል፡፡ በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ወር የክረምት ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ እና እየተጠናከረ የሚሄድበት ጊዜ ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የተሻለ ዝናብ መጠንና ስርጭት ይስተዋላል። በወሩ በመደበኛው ሁኔታ የሚጠበቀው አማካይ የዝናብ መጠን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ ስፍራዎች ላይ ከ200-500 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ18-27 ቀናት ያህል ይዘንባል። በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን ከ60-200ሚ.ሜ የሚደረስ ዝናብ ከ6-21 ቀናት ያህል ይዘንባል፡፡ ከክረምት ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በጁላይ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ከ30 እስከ 50% የሚሆነውን የወቅቱን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ።

### 2.1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ወር በብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ እና እየተጠናከረ የሚሄድበት ጊዜ ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ነጎድጓዳማና በረዶ አዘል ዝናብ ይኖራል፡፡ በተጨማሪም የዝናቡ ጥንካሬም ለረጅም ሰዓታት ያለማቋረጥ የሚዘንብበት ወር ነው፡፡

በመጪው የጁላይ ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች እየተጠናከሩ የሚመጡበት ወር ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳትም የጎርፍ ተጋላጭ በሆኑት እና በከተሞች አከባቢዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአህዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡


በአጠቃላይ በሚቀጥለዉ ወር ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ ዋግ ህምራ፣

Ethiopian Meteorology Institute



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

የሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ ፓዌ፤ አሶሳ፤ ካማሺ ዞኖች እና ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፤ ከጋምቤላ ክልል ንዌር፣ አኝዋክ፣ ማዣንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ከዕለት ወደ ዕለት ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ገጽታዎች ላይ በመነሳት፣ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ጀራር፣ ኤረር፣ ኖጎብ፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ፣ ጋቢ፣ ማሂ እና ሀሪ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ባስኬቶ፣ ጌድዮ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-31፣ 2025 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2.2 እ.አ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የጁላይ ወር በአብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጠበቀው ከቀላል እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበትን የሚያሻሽል ከመሆኑ አንፃር ዘር ለመዝራት፣ አስቀድመው የተዘሩና በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች እድገት፣ ለቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንዲሁም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእፅዋት ልምላሜና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል ከክረምት ዝናብ መጠናከር ጋር ተያይዞ ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ እና በመደበኛ ባህሪያቸው በእርጥበት መብዛት በሚታወቁ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ከመጠን በላይ ሊሆን ስለሚችል በዚህም ምክንያት ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣት፣ የማንጣፈፍና የመከላከል ስራ በመስራት እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች ከእርጥበት መብዛት ጋር የአረም መከሰትና የሰብል ተባይ መፈጠር ሊኖር ስለሚችል ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ የቅድመ ጥንቃቄ ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የማደበሪያና ጸረ-ተባይ ኬሚካሎችን አጠቃቀም የዝናቡን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ማከናዎን ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል የሚጠበቀው እርጥበት በደርሱ የበልግ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ በመካከል በሚገኙ ደረቅ ቀናት የሰብል ስብሰባን ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልልል፡፡

## 2.3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የጁላይ ወር በአብዛኛው ተከዜ፣ መረብጋሽ፣ አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው እና የመካከለኛ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም የአዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት የሚኖራቸው ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ተፋሰሶች በቂ ውሃ እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ከሚኖረው ተደጋጋሚ የሆነ ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በተለይም ጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ የከተማም ሆነ የገጠር አካባቢዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ እና የወንዞች ከፍታ መጨመር ሊያስከትል ይችላል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የጎረፍ ስጋትን ለመቀነስ የጎርፍ የፍሳሽ መውረጃዎች ቦዮችን ማፅዳት እና የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀትእንዲሁም የሚኖረውን መልካም ዕድሎችን በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የዝናብ ውሀ ማሰባሰብና የማጠራቀም ተግባራትን ለማከናውን አስፈላጊ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ከወዲሁ ማከናወንያስፈልጋል።



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et